# ሰጥቶ መቀበል የወለደው አዲስ መንፈስ!

ከሃብሮማይ
ghabrom@yahoo.com

አንድ አገር ጠንካራ የዴሞክራሲ ግንባታ ለማካሄድ ከፈለገች ብዙህነትን (pluralism) መቀበል ይኖርባታል፡፡ አገሮች የተለያየ የመልክዓ ምድር አቀማመጥ፣ ባህል፣ እምነት፣ ወግ፣ ቋንቋ ወዘተ...ስላላቸው ከዚህ በመነጨ የተለያዩ ፍላጎቶች መኖራቸው አይቀሬ ነው፡፡ የተለያየ ቋንቋ፣ እምነት ...ያላቸው አገሮች ወይም አንድ ዓይነት ሃይማኖትና ቋንቋ ያላቸው አገሮችም አንድ ዓይነት ፍላጎት አላቸው ማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም እንደ አገር እንተወውና እንደ ቡድንም ግለሰብም የተለያዩ ፍላጎቶች አሉን፡፡ ስለሆነም ነው ለአንድ አገር ዴሞክራሲ፣ ብዙህነት ምሰሶ ነው የሚባለው፡፡

ብዙህነትን መቀበል ማለት ዞሮ ዞሮ የተለያዩ ፍላጎቶችን በዴሞክራሲያዊ አኳኋን ማስተናገድ ማለት ነው፡፡ ይዴሞክራሲን ባህል እውን ባደረጉ አገሮች የተለያዩ ፍላጎት ያላቸው ፓርቲዎች መፈጠራቸው አይቀርም፡፡ የነዚህ ፓርቲዎች ዋና ዓላማ በዴሞክራሲያዊ መንገድ በህዝብ የተመረጠውን መንግስት ያሉትን ጠንካራ ጎኖች የሚያጎለብቱበት፣ ደካማ ጎኖችን ደግሞ የሚተቹበት በአጠቃላይ በአገራዊ ጉዳይ ላይ በፖለቲካ ሕግ ጨዋታ የሚፋጩበት መድረክ ነው፡፡ መንግስትም ችግሮቹን አይቶ የማስተካከል እርምጃ የሚወስድበት ለሃገርና ለህዝብ ጠቃሚ ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችለው እድል የሚፈጠርበት ነው፡፡

ይህ ሊሆን የሚችለው መንግስትና ተቃዋሚ ፓርቲዎች አንድ የሚያደርጋቸውና የሚያስማማቸው አገራዊ ስለሚኖር ነው፡፡ አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ከሌለ ስለ ጋራ ጉዳይ ማሰባቸው ይቀራል፡፡ በዴሞክራሲ የዳበሩ አገራት ገዢው ፓርቲና ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚጋሩት ጉዳይ አለ፡፡ እሱም በህዝባቸው ተሳትፎ እውን የሆነው የቃል ኪዳናቸው ሰነድ የሆነው ሕገ

መንግስታቸው ነው፡፡ ሁሉም ፓርቲዎች ለዚህ ሰነድ ተገዢ መሆናቸው ህግና ስርዓት በሃገራቸው የበላይ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

ስለሆነም በጨዋታው ሕግ መሠረት ምንም ቢፋጩና ቢተቻቹም በአገራቸው ደህንነት ጉዳይ ግን የጋራ የሆነ ስምምነት አላቸው፡፡ ሕገ መንግስታቸው የሁሉም ሕጎች የበላይ መሆኑን ከመቀበል ባሻገር መንግስትም ተቃዋሚዎችም ያለ ምንም ማመንታት ይህንኑ ያከብራሉ፤ ያስከብራሉ፡፡

እንዲህ ስለሆነም ነው እንግሊዛዊው ገጣሚ ዊልያም ብሌክ በመፅሐፉ ስለ ተቃዋሚዎች ሲገልጽ “መቃወም ጥሩ ጓደኝነትን ይፈጥራል” ብሎ የተናገረው፡፡ በእርግጥም በብሔራዊ ጉዳይ ላይ ስምምነት ያላቸው አገራት የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚቃወሙትም ሆነ የሚደግፉት ከራሳቸው ፍላጎት ተነስተው ሳይሆን ከህዝባቸውና አገራቸው ጥቅም አኳያ ነው፡፡

ስለመጪው ምርጫ 2002 ስናስብ ካለፈው የ 97ቱ ምርጫ ትምህርት ተወስዶ፣ በዚያን ጊዜ የነበሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች በማጤን፣ ጠንካራውን በበለጠ እንዲጎለብት በማድረግ፣ ደካማውን ደግሞ እንዳይደገም አሽቀንጥሮ በመጣል፣ መጪውን ምርጫ ከየትኛውም ጊዜ በተሻለ ሰላማዊ ፣ፍትሃዊ፣ታማኝና ነፃ እንዲሆን ጥረት መደረግ እንዳለበት እሙን ነው፡፡

ሰሞኑን በአራቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ኢህአዴግ፣ መኢአድ፣ ኢዴፓና ቅንጅት በስነምግባር ደምብ ዙርያ የተደረገውን ስምምነት በአገራችን ታሪክ አዲስ ምዕራፍ መክፈቱ የሚያሳይና መጪው ምርጫ ሰላማዊ፣ ፍትሃዊ፣ ነፃና በህዝብ ዘንድ ተአማኒነትን ያተረፈ እንዲሆን ትልቅ ምሰሶ ነው ካልኩ ያጋነንኩ አይመስለኝም፡፡

አገራችን ባለፈው ምርጫ 97 ያሳለፈችውን ሁከትና ብጥብጥ ዳግም ላይመለስ ይህ የስነምግባር ደንብ ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ በምርጫ 97 ተቃዋሚ ፓርቲዎቻችን የስነምግባር ደንብ ባለማዘጋጀታቸው

ብሎም ለአባሎቻቸው በስነምግባር ዙርያ ባለማወያየታቸው የተነሳ አላስፈላጊ ሕገወጥ እንቅስቃሴዎች እንዲከሰቱ ምክንያት እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡ በመሆኑም ፓርቲዎቻችን ካለፈው ትምህርት ወስደው መጪው ምርጫ እንከን የለሽ ለማድረግ የሚያስችል ደንብ መፈራረማቸው ለሰላም ወዳዱ የኢትዮጵያ ህዝብ ትልቅ ብስራት ነው፡፡

የአገሪቱ ኢኮኖሚ ባለፉት 6 ዓመታት በሁለት አሃዞች እድገት ማስመዝገቡ ይታወቃል፡፡ ይህንን ዕድገት ቀጣይነት እንዲኖረውና ህዝቡ በሰራው ሰራ መጠን እያገኘው ያለው ጥቅምም ከፍ እያለ እንዲሄድና ቀጣይነት እንዲኖረው ሰላምና መረጋጋት ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የስነምግባር ደንብ መጪውን ምርጫ ሰላማዊ እንዲሆን የማይተካ ሚና ስለሚኖረው የፖለቲካ ፓርቲዎቻችን ይህን የተቀደሰ ተግባር ደግፈው ሰጥቶ በመቀበል መርህ በመወያየትና በመቻቻል ከሁለት ወር በላይ የፈጀ ድርድር አካሂደው ለውጤት መብቃታቸው፣ መጪው የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ የሰላም ነፋስ የሚነፍስበት እንዲሆን ያደርገዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡ በአገራችንም የድርድር ፖለቲካ ስር እየሰደደ እንደመጣ አመላካች ነው፡፡

ይህን የስነምግባር ደንብ አጠቃላይ ይዘቱ ሲታይ በሕገመንግስቱ የተቀመጡ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሳይሸራረፉ ተግባራዊ የሚሆኑበትን አቅጣጫ የቀየሰ በመሆኑ አራቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይህንን ደንብ አምነው ተቀብለው ማፅደቃቸው ለአገሪቷ ሕገ መንግስት ያላቸውን የፀና እምነት የሚያሳይ ነው፡፡ ሕገ መንግስቱን መሰረት አድርገው የሚወጡ ሕጎች ደግሞ ለአገሪቷ የዴሞክራሲ ስርዓት መጎልበት ወሳኝ ሚና እንዳላቸው የሚያጠያይቅ አይመስለኝም፡፡

ካለፉት ሶስት ዙሮች ከተካሄዱ አገር አቀፍ ምርጫዎች ትምህርት በመውሰድ አራተኛው አገር አቀፍ ምርጫም ሆነ ወደፊት በአገራችን የሚካሄዱ ምርጫዎች ሁሉ በላቀ ደረጃ ግልፅ፣ ነፃ፣ ዴሞክራሲያዊ ፣ የህዝብ ተሳትፎ የጎላባቸው፣ ተቀባይነት ያላቸውና ሰላማዊ እንዲሆኑ ለማድረግ ይህ

የስነምግባር ደንብ ትልቅ አስተዋፆ ይኖረዋል ብየ አስባለሁ፡፡ በመሆኑም ይህንን የተቀደሰ ዓላማ በስምምነት መጠናቀቁ ትልቅ ነገር ሆኖ ፓርቲዎቹ ይህንን ስምምነት ወደ ተግባር ለመቀየር ግን ብዙ ስራ እንደሚጠበቅባቸው ማወቅ ይገባቸዋል፡፡

ያለፈውን የ’97 ምርጫ ሰላማዊ እንዳይሆን ካደረጉት አንዱና ዋነኛው ምክንያት ተቃዋሚዎች የስነምግባር ደንብ አለማዘጋጀታቸው፣ አባሎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ከምርጫ ስነ ምግባር ውጪ በሆነ ሁኔታ እንዲንቀሳቀሱ እድል ስለሰጣቸው ሃገራችን ለሁከትና ትርምስ እንደዳረጓት የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ ለዚህ አስከፊ ውጤት መነሻ የነበሩት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ግልፅ የሆነ የፖለቲካ ፕሮግራም አለመያዝ፣ ሽንፈትን በፀጋ አለመቀበል፣ የመቻቻል አቅም ዜሮ መሆን፣ አደገኛ የፕሮፓጋንዳና የኮሚዩኒኬሽን ስልት መከተል፣ ሂስና ነቀፌታ ለመቀበል ዝግጁ አለመሆን፣ ልዩነትን ወደ ጥላቻ መቀየር፣ አባልን በዓላማ ከማሰባሰብ ይልቅ በስሜትና ባልሆነ መረጃ ማቅረብና ማራቅ፣ በገንዘብ ዙሪያ ምግባረ ብልሹነት፣ እርስ በርስ መወነጃጀል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በምርጫ 97 ገዢው ፓርቲ ለአባሎቹና ለደጋፊዎቹ የስነምግባር መርሆች አዘጋጅቶ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ገዢው ፓርቲ ብቻ የስነምግባር ደንብ በማዘጋጀቱ ምርጫው ሰላማዊ ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ ትንሽ ነው፡፡ ምክንያቱም በአገራችን ብዛት ካላቸው ፓርቲዎች አንድ ፓርቲ ብቻ የስነምግባር ደንብ ለአባላቱና ደጋፊዎቹ በማዘጋጀቱ የ97 ምርጫ ሰላማዊ እንዲሆን ሊያደርገው የሚችል አልነበረም፡፡ ነገር ግን የገዢው ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች የስነምግባር ደንቡ የተሻለ ግንዛቤ ስለነበራቸው መረን የለቀቀ አደገኛ የኮምዩኒኬሽን ስልት ሲጠቀሙ አልተስተዋሉም፡፡ ይህ ደግሞ ገዢው ፓርቲ ለአባሎቹ ያዘጋጀውን የስነ ምግባር መመሪያ ውጤት ነበር፡፡ የገዢው ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች በዛ ጊዜ እንደነበሩ ተቃዋሚዎች በስነምግባር ደንብ ሳይገዙ አደገኛ የኮምዩኒኬሽን ስልት ተጠቅመው ቢሆኑ

ኖሮ አገሪቱ ወደማያባራ ብጥብጥ ልትገባ ትችል እንደነበር በቀላሉ መገመት ይቻላል፡፡

ያለፈው አልፏል እነሆ አሁን አገሪቷ አራተኛ አገር አቀፍ ምርጫ ለማሰተናገድ ደፋ ቀና ማለት ጀምራለች፡፡ መጪው ምርጫ ሰላማዊ፣ ፍትሃዊ፣ ነፃና በህዝብ ዘንድ ታማኝ እንዲሆን አራቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች አመራሮቻቸውና አባሎቻቸውን የሚገዛ የስነምግባር ደንብ በጋራ በመፈራረም ታሪካዊ ስራ ሰርተዋል፡፡ መፈራረም ብቻ ግን ግብ አይደለም፡፡ ሁሉም የፓርቲ አመራሮች ለአባሎቻቸውና ለደጋፊዎቻቸው የስነ ምግባር ደንቡን ማሳወቅና ለደንቡ ተገዢ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል እላለሁ፡፡

ይህን ስናደርግ ነው ለአገሪቷ ሰላም፣ መረጋጋትና ልማት ትልቅ አስተዋፅኦ አበረከትን የምንለው፡፡ እነዚህ አራቱ ፓርቲዎች መጪውን ምርጫ ሰላማዊ ለማድረግ በፊርማቸው ሲያረጋገጡ የኢትዮጵያ ህዝብ ደስታና እርካታ እንደተሰማው ሁሉ በተግባር ሲተረጉሙት ደግሞ ህዝቡ ድርብ ደስታ ያደርጋልና ጠንክረው መስራት ይጠበቅባቸዋል የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

አሁን ቁልፍና ዋነኛ ተግባራቸው ይህንን የተስማሙበት ሰነድ መላው አባላቸው ጠንቅቆ እንዲያውቀው ማድረግ ነው፡፡ አራቱ ፓርቲዎች ይህንን የስነምግባር ሰነድ ለአባሎቻቸው በሚገባ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ካደረጉ ወደ ተግባር ለመተርጎም ብዙም የሚከብድ ስለማይሆን በአባሎቻቸው ብሎም በደጋፊዎቻቸው ዙርያ ጠንክረው መስራት ይጠበቅባቸዋል እላለሁ፡፡ በስምምነቱ ትኩረቴ የሳበው ጉዳይ ካለ በተወካዮች ምክርቤት ቀርቦ የአገሪቱ ሕግ ሆኖ የሚወጣበት ዕድል ማመቻቸታቸው ነው፡፡ ይህ ማለት አራቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ ሳይሆን በሙሉ የአገራችን ፓርቲዎች የሚገዙበት ሰነድ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ይህ ታሪካዊ ውይይት አዲስ የመደማመጥ የፖለቲካ ጅማሬ ኢህአዴግ ያቀረበውን ዓለም አቀፋዊ የስነምግባር ደንብ ትርጉምና መኢአድ

የጋናና የደቡብ አፍሪካን ልምድና የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ ያቀረባቸውን ሰነዶች እንደ መነሻ ተቀብለው ኢዴፓና ቅንጅትም በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ያላቸውን ገንቢ ሃሳብ እያዋሃዱ እንዲሄዱ በመስማማት ባደረጉት ውይይትና ድርድር እነሆ አራቱ ፓርቲዎች ሰጥቶ የመቀበልን መርህ ተግባራዊ በማድረግ በጋራ የሚታገሉላቸው ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የስነ ምግባር ደንብና አፈፃፀም መመሪያ ለማፅደቅ በቅተዋል፡፡ ይህ ደግሞ ለአገራችን ፖለቲካ አዲስ ባህል የሆነውን የድርድር ፖለቲካን ማዳበር መጀመሯን የሚያበስር ነው፡፡ ይህ ደግሞ አዲስ የሰላም ሃዋህውና አዲስ መንፈስ ፈጥሯል የሚል እስተያየት አለኝ፡፡

ይሁን እንጂ መድረክ የተባለው የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ የስነ ምግባር ውይይት ለመካፈል ዝግጁ ባለመሆኑ የተለያዩ ቅደመ ሁኔታዎችን በመደርደር ራሱን ከሌሎች ፓርቲዎች በላይ በመቁጠር ስብሰባውን ረግጦ መውጣቱ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ ይህ የስምንት ፖለቲካ ፓርቲዎችና ሁለት ግለሰቦችን ያቀፈው ፓርቲ በዚህ ታሪካዊ ምዕራፍ ለመካፈል ፍላጎት እንደሌለው የተለያዩ ሰንካላ ምክንያቶችን በመደርደር ከዚህ ድርድር ራሱን አግልሏል፡፡ መጪው ምርጫ ሰላማዊ፣ ፍትሃዊ፣ ታማኝና፣ ነፃ ለማድረግ እንዲቻል የምርጫ ስነምግባር ደንብ ዋነኛ መሳርያ ነው፡፡ መድረክ ግን ይህንን ዓላማ ለማሳካት በድርድሩ እንዲሳተፍ በተደጋጋሚ ተጠይቆ አሻፈረኝ ማለቱን ቀጥለውበታል፡፡ ይህ የሚያሳየው ደግሞ መጪውን ምርጫ ሰላማዊ እንዳይሆን ካለው ፍላጎት የመነጨ ነው ብል ያጋነንኩ አይመስለኝም፡፡ ይሁን እንጂ መድረክ አሁንም ወደ ድርድሩ የሚገባበትን ዕድል እንዳለው ነው የሚነገረው፡፡ አሁንም ጊዜው አልመሸምና መድረክ ይህንን ዕድል ተጠቅሞ ቀሪውን ድርድር ተቀላቅሎ ሰጥቶ በመቀበል መርህ ምክንያታዊ በሆነ አካሄድ በአራቱ ፓርቲዎችየፈነጠቀውን ሰላማዊ ነፋስ ተጋሪ በመሆን መጪውን ምርጫ ሰላማዊ እንዲሆን የራሱን ድርሻ መወጣት አለበት እላለሁ፡፡

ይህ ሰፊ ውይይት ተደርጎበት የተዘጋጀው ሰነድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባለው የዴሞክራሲና የምርጫ ዓለም አቀፍ ኢንስቲትዩት

(IDEA) ሞዴል የተከተለ በመሆኑ የሰነዱን ተቀባይነት የጎላ ያደርገዋል፡፡ በድርድሩ ወቅትም የኢምባሲዎችና የአምባሳደሮች ስብስብ የሆነውን የኢትዮጵያ አጋሮች ቡድን (EPG) በታዛቢነት በመገኘታቸው በአገራችን ያለውን የመድብለ ፓርቲ ስርዓት በደንብ እንዲያውቁ ረድቷቸዋል፡፡

ለዚህም ነው በፖለቲካ ፓርቲዎቹ የተፈረሙ የምርጫ ስነ ምግባር ደንብ ሰነድ ሰላማዊ፣ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ማካሄድ ላይ የተመሰረተና ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን በኢትዮጵያ የኢንግሊዝ አምባሳደርና በአፍሪካ ህብረት የእንግሊዝ ቋሚ ተወካይ የሆኑት አምባሳደር ኖርማን ሊንግ አስረግጠው የተናገሩት፡፡ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ሚድያዎቹም የሰነዱ መፈረም ለምርጫው ቀና እንደሆነ የዘገቡት፡፡

በመሆኑም መጪው ምርጫ ሰላማዊ፣ ፍትሃዊ፣ ነጻና በህዝብ ዘንድ ታማኝ እንዲሆን ከፓርቲ አመራሮች፣ አባሎችና ደጋፊዎች በተጨማሪ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን የስነ ምግባር ደንብ ስምምነት የፈጠረውን አዲስ መንፈስ ተግባራዊ ለማድረግ በሚችለው ሁሉ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅበታል እላለሁ፡፡